# አጭር የኢትዮጵያ ታሪክ

## ከንግሥተ ሳባ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ

------/------

ከምርመራና ከሥርዓት ትምህርት ዲሬክሲዮን

-------------

ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር

፲፱፻፵፩ እ.ኤ.አ.

ተለጣጣቂ መጻሕፍት

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# አጭር የኢትዮጵያ ታሪክ

## ከንግሥተ ሳባ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ

------/------

ከምርመራና ከሥርዓት ትምህርት ዲሬክሲዮን

-------------

ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር

፲፱፻፶፩ ዓ.ም.

ተለጣጣቂ መጻሕፍት

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት
ዘኢትዮጵያ።

***ሀ.*** «--- የሀገራችንን ትምህርት ሳይማሩ የውጭ አገርን ዕውቀት እማራለሁ ማለት በድቡሽት ላይ ቤት

እንደሠራው ሰው መሆን ነው ---»

**ለ.** እና የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት መንግሥት ቋንቋ አማርኛ ነው። ሕዝቡም ከዳር እስከ ዳር ሥልጣኔን

ለመቀበል የሚችለው በራሱ ቋንቋ ሲያስተምሩት ነው። ስለዚህ ከዚህ ቀደም ሲሠራበት በኖረው

የአጻጻፍ መሠረት አንድ አጭር የኢትዮጵያ ታሪክ «ከንግሥተ ሳባ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ» በሚል አርእስት ሕፃናት በገዛ ራሳቸው ቋንቋ አንብበው እንዲነቃቁና እንዲጠቀሙ አዘጅተንላቸዋል።

## ማውጫ

መቅድም5

ንግሥተ ሳባ6

የአክሱም ሥልጣኔ8

የክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባት11

የፖርቱጋል ወደ ኢትዮጵያ መግባት14

ኢማም አህመድ ግራኝ18

አቡነ ተክለ ሃይማኖት21

ጎንደር24

አፄ ቴዎድሮስ27

አፄ ዮሐንስ32

ዳግማዊ ምኒልክ35

# መቅድም

ይህ አጭር ታሪክ ለልጆች በሚመጥን ሁኔታ ከግዕዝና ከአማርኛ መጻሕፍት እየተመረጠ ተዘጋጀ። ቃላቱ እንዳይከብዱና ልጆቹን እንዳያስቸግሯቸው በልጆች ደረጃ እቀላል ተዘጋጅቷል። መጽሐፉ የኢትዮጵያን ታሪክ በዝቅተኛ ክፍሎች በዝርዝር ለማስተማር አይሞክርም። ነገር ግን ለወደፊት ለማጥናት የሥራ መንቀሳቀሻና መምሪያ ይሆናቸዋል።

ታሪኩ ከንግሥተ ሳባ ጀምሮ በዳግማዊ ምኒልክ ይጨርሳል። ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔና ታላላቅ መሪዎች በመጠኑ ይተርካል። በሃይማኖት በኩልም ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገባ ይገልጻል። እንደዚሁም የቤተክርስቲያንና የሕዝቡን ርምጃ እንዴት ያለ አደገኛ እንቅፋት ገጥሞት እንደነበረና በውጪ አገር ክርስቲያኖች ርዳታ እንደገና እንሠራርቶ በሙሉ ጫማውም እንደቆመ ያመለክታል።

በጠቅላላ የዚህ አጭር ታሪክ የአጻጻፍ ስልት ከዚህ ቀደም ከተጻፉት መጻሕፍት ጥቂት ለየት ይላል። ታሪኩ ነገሥታቱን ሕዝቡና የሃይማኖት መሪዎችን አዋሕዶና አስተሳስሮ ያቀርባቸዋል። ስለዚህ የጦር ታሪክን ብቻ ባለመሸከሙ በመግቢያነት የሚያቀርበው ተግበር ባለ ሚዛን ነው።

# ንግሥተ ሳባ

ንግሥተ ሳባ በዓለም ታሪክ ውስጥ በጣም የታወቀች የኢትዮጵያ ንግሥት ናት። ንግሥተ ሳባ ከክርስቶስ ልደት በፊት በአክሱም ተወለደች። አባትዋ ተዋስያ የተባለ የክሱም ንጉሥ ነበር።

እርሷም በልጅነቷ የጊዜውን ሕገ መንግሥትና ደንብ አጠናቃ ተማረች። አባቷ ተዋስያ ሲሞት ዙፋኑን ወረሰች። ንግሥተ ሳባ በጣም ሃሳበ ሰፊና በሕዝቡም ዘንድ ስመ ጥሩ ንግሥት ሆነች። እርሷም የኢትዮጵያ ግዛት በዘመኗ ለማስፋፋት ትልቅ ምኞት ነበራት። ስለዚህ ከምሥራቅ አገሮች ጋር ግንኙነትና ወዳጅነት ማድረግ ጀመረች። የኢትዮጵያንም ግዛት ከየመን እሰከ ማዳጋስካር ድረስ አስፋፍታ ነበር ይባላል በአክሱም ብዙ የታሪክ ሥራዎች እንደፈጸመች ይነገራል።

ንግሥተ ሳባ በወንጌል ውስጥ ንግሥተ አዕብ በክብረ ነገሥት ደግሞ ንግሥት ማክዳ ትባላለች። ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ ግዛትዋን አስፍታ በመሬትና በባሕር ላይ ልዩ ልዩ ሸቀጣ ቀሸጥ ትነግድ ነበር። በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ መርከቦች እሰከ ሰባ ይሆኑ ነበር ይባላል። በዚያን ዘመን ኢትዮጵያ ከሠለጠኑት አገሮች ጋር ግንኙነት ስለነበራት እርሷም የሠለጠነች ነበረች። የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ወደ ሩቅ አገር እየሄዱ ይነግዱ ነበር። ታምሪን የተባለ ነጋዴም እሰከ ኢየሩሳሌም ድረስ እየሄደ ይነግድ ነበር ይባላል። እርሱም ከኢየሩሳሌም ሲመለስ ስለሰሎሞን ብልኀነትና ጥበብ ለንግሥተ ሳባ ነገራት። ንግሥተ ሳባም የሰሎሞንን ጥበብ በሰማች ጊዜ ጥበቡን ለማየት የጋለ መንፈስ አደረባት።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ብዙ ሰውና ጓዝ አስከትላ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች። እርሷም ኢየሩሳሌም ስትደርስ የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን በክብር ተቀበላት። ንግሥተ ሳባም በንጉሥ ሰሎሞንና በጥበቡ በጣም ተደሰተች። ንግሥተ ሳባ በጣም ቆንጆና ንግግረ መልካም ነበረች። ከዚህም የተነሣ ንጉሥ ሰሎሞን በመልኳ ውበትና በአነጋገሯ ልዝብነት ኅሊናው ተማረከ።

ስለዚህ ንግሥተ ሳባ የፍቅር ጓደኛው እንድትሆን ለመናት። እርሷ ግን ድንግል ስለነበረች ለጊዜው እንቢ አለች። በኋላ ግን ንጉሥ ሰሎሞን ልዩ ብልኅት ፈልጎ ኀሳቡን እንደፈጸመ ይናገራል። እርሷም በዚያን ሌሊት

ቀዳማዊ ምኒልክን ፀነሰች። ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሥ ዘር ከሰሎሞን ዘር ተደባለቀ።

ይሁንና ንግሥተ ሳባ ወደ መናገሻ ከተማዋ ስትመለስ ይናፍቃት የነበረው ሕዝብ በደስታ ተቀበላት። ከንጉሥ ሰሎሞን የፀነሰችውንም አገሯ ከተመለሰች ከጥቂት ወራት በኋላ ወንድ ልጅ ወለደች። ስሙንም ምኒልክ አለችው። ትርጉሙም የንጉሥ ልጅ ማለት ነው ይባላል አንዳንዶቹ ደግሞ ልዩ ትርጓሜ ይሰጡታል፡ ንግሥተ ሳባ የኢትዮጵያን ግዛት አስፋፍታ ብዙ ዓመታት ከገዛች በኋላ ሞታ በአክሱም ተቀበረች። በመቃብሯም ላይ 24 ሐውልቶች ቆመው ነበር። ዛሬ ሐውልቶቹ በሙሉ ተሰባብረው አርጅተው አልቀዋል።

ንግሥተ ሳባ የኢትዮጵያ ተወላጅ አይደለችም የሚሉ ታሪክ ጸሐፊዎች ይገኛሉ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ንግሥት እንደነበረች በሀገራችን በሰፊው የታመነ ነው። ያም ሆነ ይህ ንግሥተ ሳባ ትልቅ ንግሥት ነበረች። ብዙዎች ታሪክ ጸሐፊዎች ባለቅኔዎች ስሟን በምስጋና ያነሥዋታል።

## ጥያቄዎች

1. ንግሥተ ሳባ በአክሱም የሠራችው ታሪካዊ ሥራ ምን ይመስላችኋላ? ባምስት መስመሮች ያህል ግለጹት።
2. ንግሥተ ሳባ በወንጌል የተጠቀሰችው በምን ምክንያት ነው? የጠቀሳትስ ማን ነው?
3. ታላላቅ መንገደኞችና ነጋዴዎች እንዴት ሊመላለሱ ይችላሉ?
4. ታምሪን እንዴት ያለ ሰው ነበር?
5. ንግሥተ ሳባ ከኢየሩሳሌም ምንን ይዛ ተመለሰች?
6. ባለቅኔዎች እንዴት ያሉ ሰዎች ናቸው?

# የአክሱም ሥልጣኔ

ኢትዮጵያ ከጌታ ልደት በፊት ከአንድ ሺ ዓመታት አንሥታ በንጉሥ የምትገዛ የጥንታዊ ሥልጣኔ አገር ነች። የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ዋና መሠረት የሆነው ታሪካዊው የአክሱም ከተማ ነው። አክሱም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣኔ የተፈጠረበት ከተማ ብቻ ሳይሆን ዘጠኝ መቶ ዓመታት ሙሉ የንጉሠ ነገሥት ከተማ ነበር። ዛሬ አክሱም ምንም እንኳ በጦርነትና በወረራ ምክንያት የሥልጣኔው ትርዕይት ቢፈርስና ቢጠፋም ለምስክር የሚሆኑ አንዳንድ የሥልጣኔ ርዝራዥ የሆኑ ሐውልቶችና የግንብ ቤቶች ይታያሉ።

ኢትዮጵያ በአክሱም ሥልጣኔ ዘመን ግዛትዋ በጣም ትልቅ ነበር ይባላል። ጠረፍዋም በስተሰሜን እስከ ቀጥ ባሕር ድረስ በስተደቡብ እስከ ዐረቢያን መሬታዊ ሰላጤና እስከ ኖባ በረሃ ድረስ ነበር ተብሎ ይገመታል። በዚያን ዘመን ኢትዮጵያ ሀብታም ነበረች። የሕዝቡም ሥልጣኔ ደረጃ ከፍ ያለ ነበር ይባለል። በዚያ ጊዜ ኢትዮጵያ በዓለም ንግድ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ይዛ እንደ ነበር ይነገራል። ብዙ የባሕር ወደቦች እንደነበርዋትም ይነገራል። ከነዚህም ጥንታውያን ወደቦች አንዱ ከምጽዋ በስተደቡብ የነበረው አዶሊስ እይተባለው እንደ ነበር ይታመናል። በአዶሊስ ወደብ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች እንደልባቸው ከመርከብ እየገቡና እየወጡ በመዲተራኒያን ባሕር ላይ ይነግዱ ነበር። ከዚህ በላይ ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ ብዙ የጦር መርከበኞች ነበሯት። ከሕንድ ከሮማና ከግሪክ አገሮች ጋር ደግሞ የምትገናኝባቸው ብዙ የንግድ መርከቦችም ነበሯት። ስለዚህ ኢትዮጵያ በአክሱም ሥልጣኔ ዘመን ከሜዲትራኒያን ዓለም ሥልጣኔ ጋር ደንበኛ ግንኙነት ነበራት ማለት ነው።

በአክሱም ሥልጣኔ ዘመን በብዙ የሚቆጠሩ ልዩ ልዩ ሐውልቶች የሥልጣኔ ትርዕይቶች በኢትዮጵያ ተሠራ። በተለይም በአክሱም ከተማ ትላልቅ ድንጋዮች ጥርቦች ተተከሉ። በነዚህም ድንጋዮች ላይ በየጊዜው የተደረጉት ሥራዎችና የበዓላት ታሪኮች ይጻፉ ነበር። እነዚህም ጥርብ ድንጋዮች ልዩ ልዩ ጌጥና የሃይማኖት ትእምርት ቅርጾች ነበሯቸው።

በአክሱም የነበሩት ሐውልቶች የድንጋይ ጥርቦች በቁመትም ሆነ በክብደት በግብጽ አገር ከነበሩት ሐውልቶችና ጥርቦች በጣም የሚበልጡ ነበሩ።

ሆኖም ብዙዎች የአክሱም ሐውልቶች በየጊዜው ፈራረሱ አሁን በቅርቡ በጠላት ወረራ ጊዜ ደግሞ የተቀሩትን አፈረሳቸው። ዛሬ ጥንታውያን የአክሱም ሐውልቶች አንዱ ብቻ እስካሁን ቆሞ ይገኛል። ይህ አስደናቂና ግሩም ሐውልት ስባ ጫማ ያህል ቁመት አለው በላይም ላይ በአክሱም የሥልጣኔ ዘመን የተሠራው ባለጠኝ ፎቅ ግንብ ቤት ምስል ተቀርጾበታል።

ከዚህም በላይ ጥንታዊው አክሱም የኢትዮጵያ ሃይማኖት የተመሠረተበት ታሪካዊ ከተማ ነው። አኩስም ሐውልቶች ላይ ተቀርጾ እንደተገኘው ከአሪት በፊት አራት መቶ ዘመናት ያህል ኢትዮጵያ ከደቡብ ዐረቢያ ቀድታ በጣዖት ታመልክ እንደነበር ይነገራል። ሆኖም ኢትዮጵያ ጣዖት በምታመልክበት ዘመን ባንድ በኩል ደግሞ እግዚአብሔርን ብቻ ማመን የአይሁድ ሃይማኖት በኢትዮጵያ በሠፊው እንደነበር ይነገራል። ይህም የይሁዳ ሃይማኖት በተለይ በአገው ተስፋፍቶ ነበር። ይህን ሃይማኖት መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ያስመጣው ቀዳማዊ ምኒልክ እንደሆነ የታወቀ ነው።

በኋላ ግን በአራቶ መቶ ዓ.ም ማለቂያ ገደማ በአኩስም የክርስቲያን ሃይማኖት ተመሥርቶ በመላ ኢትዮጵያ ተስፋፋ ይህም የሆነው በአብርሃና አጽብሐ የተባሉ ወንድማማቾች በኢትዮጵያ በነገሡበት ዘመን ነው። እነርሱም የክርቲያን ሃይማኖት አምነው መጀመሪያ ተቀበሉ። ከዚህም በቀር ኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የተጀመረው በአኩስም የሥልጣኔ ዘመን ነው። ሐዲስና ብሉይ በዚሁ በአምስተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ገደማ ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተተረጐመ። በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ እንደምናገኘው አዲስንና ብሉይን የተረጐሟቸው ከሶርያ የመጡ ዘጠኙ ቅዱሳን ናቸው። እነሩም በቤተ ክህነት ታሪክ «ዘጠኙ ቅዱሳን» እየተባሉ ይከበራሉ።

ይህ የአኩስም የሥልጣኔ ዘመን የሚባለው የተጀመረው በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው ይባላል። ይህም የአኩስም ዘመን እስከ አሥረኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ ከቆየ በኋላ ተፈጸመ። ዮዲት

የምትባል ክርስቲያን ያልሆነች ንግሥት ተነሥታ የአክሱምን ንጉሥ ዙፋኑን ቀማችው። ከዚህ በኋላ የአኩስምን ቤተ ክርስቲያኖችና ሐውልቶች ሁሉ አቃጠለች። ሕዝቡንም ባሪያ አደረገችው። በዚያን ጊዜ የአኩስም ንጉሥ የነበረው አንበባ ውድም ነበር። እሱም ገና ሕፃን ስለ ነበር ዮዲትን ሊወጋ አልቻለም። ስለዚህ ወደ ሸዋ ሸሽቶ መንዝ ውስጥ ገብቶ ተቀመጠ። ዮዲትም የአኩስም ዙፋን ቀምታ ዓርባ ዓመታት ሙሉ በጭቆናና በግፍ ገዝታ ሞተች።

ዮዲት ከሞተች በኋላ አንበባ ውድም ወደ አኩስም ተመልሶ እንደገና ነገሠ። እርሱም ጥቂት ዓመታት ከገዛ በኋላ ሞተ። ዙፋኑንም ልጁ ድልናድ ወረሰ። ነገር ግን የላስታው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከዮዲት ወገኖች ጋር ተባብረው አኩስምን ንጉሥ ድልናድን ወጉት በመጨረሻም ድል አድርገው የአኩስምን የነገሥታት ግንድ አጥፍተው የዛጉዌ የነገሥታት ግንድ የተባለውን መሠረቱ።

ይህም የዛጉዌ ዘር ዘመነ መንግሥት 345 ዓመታት ያህል ኖረ። በዚሁ ዘመን ውስጥ የመንግሥቱም ዋና መናገሻ ከተማ ከአኩስም ወደ ላስታ ዞረ። አኩስም የነገሥታት መዲና መሆኗ ብታቋርጥም የታሪክ ምንጭነቷ እንደ ገነነ ይኖራል።

# ጥያቄዎች

1. አኩስም ከሌሎች ከተሞች በምን ትለያለች?
2. የኢትዮጵያ ታሪካውያን ቦታዎች እነማን ናቸው?
3. ተከታዮቹን ቃላት አብራራቸው:-
   ሀ. ወደብ ለ. ሐውልት ሐ. ሐዲስ መ. ብሉይ
4. የአይሁድ ሃይማኖት እንዴት ያለ እንደሆነ በመጠኑ ግለጽ
5. ክርስትና መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ በየትኛዋ ከተማ ተሰበከ?
6. ዮዲት ስለምን ጉዲት ተባለች?

# የክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባት

ኢትዮጵያ እንደ ጥንታውያን አገሮች ሁሉ መጀመሪያ በጣኦት በጨረቃና ግዙፍ በሆኑ ነገሮች ብዙ ዘመን ታመልክ ነበር። በሩቅ ምሥራቅ ስለተፈጠሩት ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ስለቡዲዝም ኮንፊዩሽኒዝም ሒንዲዩዝም አልሰማችም። በኋላ ግን በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከኢየሩሳሌም መምህራን መጥተው ኦሪት ተሰብኮ ኢትዮጵያ ብሉይን ማለት የአይሁድን ሃይማኖት /ጁዳይዝም/ አምና ብዙ ጊዜ እንዳሳለፈች ይነገራል።

ከጌታ ልደት 327 ዓመታት በኋላ ግን ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ይህን ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የሰበኩት ፍሬምናጦስና ኦዲስየስ የተባሉ የግሪክ ተወላጆጆች ነበሩ። /ኦዲስየስ በዕድሜ ከፍሬምናጦስ ያንስ ነበር።/ እነሱም የክርስቲያንን ሃይማኖት ትምህርት ሜሮፒየስ ከተባለ የግሪክ ፈላስፋ ከልጅነታቸው ጀምረው ተማሩ። ሜሮፒየስ ሁለቱን ልጆች ይዞ በመርከብ ወደ ሕንድ አገር ተጓዘ። ከሕንድ አገር ሲመለሱ በቀይ ባሕር ወደብ አጠገብ ለማረፍ ውኃ ለመቅዳት መርከባቸውን አቆሙ። በወደቡ አካባቢ የሚኖሩ ዘላን አሕዛብ መርከቧን ዘርፈው ሜሮፒየስንና በውስጡ የነበሩትን ካንድ ዛፍ ሥር ተሸሸጉ። በኋላም ደኅና ሰዎች አግኝተዋቸው በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ ነበረው ወደ ሌላ ዘንድ ቀረቡ።

ንጉሥ ኤላም ኦዲስየስ ብልኀና የደስ ደስ ያለው ልጅ በመህኑ በቤተ መንግሥት ውስጥ አሳላፊ አደረገው። ፍሬምናጦስ ደግሞ አተዋይና ረጋ ያለ ስለሆነ የቤተ መንግሥቱ ጸሐፊና የግምጃ ቤት ኃላፊ እዲሆን ሾመው። ንጉሥ ኤላ በጣም አርጅቶ ነበር። ሁለት ትናንሽ መንታና መልካቸውም የሚመሳሰል ወንዶች ልጆጆች ነበሩት። ፍሬምናጦስና ኦዲስየስ ለንጉሡ ልጆችና ሚስት በጣም ወዳጆች ሆኑ።

ስለዚህ ንጉሡ ሲሞት ልጆች እስኪያድጉ ድረስ ፍሬምናጦስ ኦዲስየስ ስለ አገር አገዛዝ የንግሥቲቷ ባለሟል ሆነው ይረዷት ነበር።

ልጆቹ አድገው ያባታቸውን ዙፋን ከያዙ በኋላ ፍሬምናጦስ ኦዲስየስ ተሰናብተዋቸው ሄዱ። ኦዲስየስ ዘመዶቹን ለመጠየቅ ወታደር ሄደ።

ፍሬምናጦስ ደግሞ ወደ እስክንድርያ ሄዶ ለአቡኑ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ሕዝቡ በሠፊው ነገረው ኢትዮጵያ በክርስቲያን ሃይማኖትና ሕግ ተደሳች መሆኗን አስረዳው። አቡነም ነገሩ በጣም ተስማው። ከዚህም በኋላ ፍሬምናጦስ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ስለ ክርስቶስና ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት እንዲሰብክ አቡኑ አዘዘው።

ከዚህ በኋላ ፍሬምናጦስ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ። አስም በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የክርስቲያን አቡን ሆነ። በቤተ መንግሥትም በትልቅ ክብር ተቀበሉት ፍሬምናጦስም ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት ንጉሣዊ ቤተሰብን መጀመሪያ አስተምሮ በኋላ ሕዝቡን አስተማረ። ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ይባል ነበር። ትርጉሙም «የሰላም አባት ማለት ነው» መጀመሪያ ክርስትናን አምነው የተቀበሉት ሳይዛናና ኢዛና የተባሉት ወንድማማች ናቸው። እነርሱም በክርስቲያን ሃይማኖት አምነው ተጠምቀው የክርስትና ስማቸው አብርሃና አጽብሐ ተባለ። የኢትዮጵያም የመጀመሪያዎቹ የክርስቲያን ንጉሦች ሆኑ።

አብርሃና አጽብሐ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በአኩስም ጽዮን ማርያም ተከሉ። ይህ ቤተ ክርስቲያን የተተከለው በ340 ዓ.ም ሲሆን በግራኝ መሐመድ ወረራ ጊዜ ፈራሰ።

ይህ ቤተ ክርስቲያን በጣም የተዋበ ነበር። ጣሪያውና ግርግዳው በቀለም ሥዕል ያጌጡ ነበሩ። እያንዳንዳቸው ቅድስት ያላቸው ሰባት ክፍሎች ነበሩት። ቤተ ክርስቲያኑ በሁለት ትላልቅ ግንቦች የተከበበ ነበር። በቤተ ክርቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ አንዱ በስተቀኝ አንዱ በስተግራ ሁለት ቤተ መንግሥቶች ነበሩ። ከሁለተኛው ግንብ መግቢያ በር ላይ አንድ ትልቅ የፈርኦን ሾላ ዛፍ የሚባል ነበር።

ክርስትና በኢትዮጵያ 200 ዓመታት ያህል ሲሰበክ ከቆየ በኋላ ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መጡ። እነርሱም ከሶርያ የመጡ የተማሩ መነኩሳት ነበሩ። በኢትዮጵያም ገዳሞች እንዲቋቋሙ ሕዝቡን አበረታቱ። እነርሱም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረቱ። ብዙ ሰዎች እየሰበሰቡ ስለ ክርስቶስ ትምህርት አስተማሩ። የክርስቶስንም ትምህርት ወደ ግዕዝ እንዲተረጐም በጣም ረዱ። ከዚህም የተነሣ ብዙዎቹ ቄሶች በደንብ የተማሩ ሆኑ። ከዚህም መካከል በቤተ ክርስቲያን ትምህርት በጣም ስሙ የታወቀ ያሬድ

ነው። ያሬድ እስከ ዛሬ ድረስ የሚሠራባቸውን በቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የሚያገለግል ልዩ ልዩ የቅዳሴ ዜማዎች አወጣ። መዝገበ ድጓ የተባለውን ትልቅ መጽሐፍ አሰናዳ።

የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ብዙ የተማሩ ቄሶች አፈሩ። ቄሶቹም በተራው ከመንደር ወደ መንደር እየተዘዋወሩ መጽሐፍ ቅዱስን አስተማሩ። ሆኖም ቄሶች ሁሉ ከግብፅ አገር ባለው በእስክንድርያ አቡን ሥር የሚተዳደሩና የሚመሩ ነበሩ። ከአቡነ አትናቴዎስ ጊዜ ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኀላፊ አቡኖች ከእስክንድርያ እየተመረጡ የየሚላኩን የባዕድ ሰዎች ነበሩ። አሁን ግን ይህ ሁሉ ቀርቶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የራሷን አቡኖች የምትመርጥ ሆናለች። በያንዳንዱም ጠቅላይ ግዛት የቤተ ክርቲያን ሁሉ ኀላፊ የሆነ አንድ አቡን ይገኛል።

## ጥያቄዎች

1. ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ ያመጡት እነማን ናቸው?
2. በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የክርስቲያን ንጉሦች እነማን ነበሩ?
3. የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን በየት ተተከለ?
4. ዘጠኙ ቅዱሳን ከየት መጡ?
5. የቤተ ክርቲያን ዜማ ለመጀመሪያ ጊዜ ማነው ያወጣ?

# የፖርቹጋል ወደ ኢትዮጵያ መግባት

ከአራት መቶ ዓመታት በፊት ፖርቹጋሎች የተባሉ የአውሮፓ ተወላጅጆች ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። እነርሱም ወደ ኢትዮጵያ ከገቡት አውሮፓውያን የመጀመሪያዎቹ መሆናቸው ነው። በዚያን ዘመን ኢትዮጵያ ፕሬስተር ጆን በሚባል ንጉሥ ትገዛ ነበር ይባላል። ይህም አፋዊ ታሪክ እንጂ እውነተኛ ነገር አይደለም። ኢትዮጵያ ከቀረው ዓለም በተለይ የሜዲትራኒያን ዓለም ከተባለው ተለይታ ብዙ ዘመን ኖረች። ይኸውም የሆነው በዚያን ዘመን ቱርክ ግዛትዋን አስፋፍታ በመያዟ ነው። ከዚህም የተነሣ አውሮፓውያን ኢትዮጵያ ወዴት እንዳለች በደንብ አያውቁም ነበር።

ቱርኮች የእስላምን ሃይማኖት ለማስፋፋት ጦርነት እያደረጉ ብዙ አገሮች ያዙ። ከዚህም የተነሣ ሰሜናዊውና ምሥራቃዊው አፍርቃ በግድም ሆነ በውድ ሰለመ። ከሜዲትራኒያን አገር ወደ አፍሪቃ ኤሽያ ያሉትን የባሕርና የእግር መንገዶች ቱርኮች ዘጓቸው። አውሮፓውያን በቱርክ ግዛት ላይ እንዳያልፉ ተከለከሉ።

በዚያን ጊዜ በአውሮፓ ውስጥ የፖርቱጋል መንግሥት በጣም ኃይለኛ ነበር፣ ብዙ መርከቦችና የሩቅ አገር ደፋር መንገደኞች ነበሩት። ከሕንድም መንግሥት ጋር የፖርቱጋል መንግሥት የንግድ ግንኙነት ነበረው። ፖርቹጋሎች ብዙ ቅመማ ቅመም ከሕንድ ያገኙ ነበር። ዳሩ ግን ቱርኮች መንገዱን ስለዘጉባቸው ከጥቅማቸው ተቋረጡ። ስለዚህ የፖርቹጋል መንግሥት ሌላ ወደ ሕንድ የሚወስድ የባሕር መንገድ መፈለፍ ግድ ሆነበት። የባሕር መንገደኛ የነበረው የፖርቹጋል መስፍን ሄንሪ አራተኛው ፕሬስተር ጆን የሚባል ኃይለኛ የክርስቲያን ንጉሥ በኢትዮጵያ መኖሩን ሰማ። ሄንሪም ከፕሬስተር ጆን ጋር ተባብሮ ቱርኮችን ለመውጋት አሰበ።

ስለዚህ ልዑል ሄንሪ የመርከብ መሪዎች ወደ ሕንድ አገር የሚወስድ የባሕር መንገድ እንዲፈልጉና ወዲያውም ስለ ኢትዮጵያ ንጉሥ ወሬ ይዘውለት እንዲመጡ አዘዛቸው። በኋላም በ1512 ዓ.ም ብዙ ፖርቹጋሎች በፍራንሲስኮ አልቫሬዝ መሪነት ወደ ኢትዮጵያ ተላኩ።

አልቫሬዝ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ብዙ ችግር በመንገድ ላይ ደረሰበት። ቱርኮች በየጊዜው መንገድ ላይ ይጣሉትና ይመልሱት ነበር። ብዙ ጊዜ መንገዱን መለዋወጥ ነበረበት። ከፖርቹጋል ከተነሣ ከሦስት ዓመታት በፊት አልቫሬዝ ከቀሩት ፖርቹጋሎች ጋር ወደ ኢትዮጵያ ገባ። የኢትዮጵያ ሰዎች በደስታ ተቀበልዋቸው። ዳፋ ግን በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበረው አፄ ልብነ ድንግል እንደ ነበረ ታሪክ ያረጋግጣል። ስለዚህ ፕሬስተር ጆን የተባለ ንጉሥ ኢትዮጵያ አልነበራትም ክርስቲያን መሆኑን ሲሰሙ በጣም ተደሰቱ። አፄ ልብነ ድንግል አልቫሬዝ ቱርኮችን ለመውጋት ስምምነት አደረጉ አፄ ልብነ ድንግል ለፖርቹጋል መንግሥት ጦር ምግብ መጠጥና ገንዘብ ወታደር ለመርዳት ቃል ገቡ። የፖርቹጋል መንግሥት ደግሞ በተራው ልዩ ልዩ የእጅ ሥራ ዐዋቂዎች ማለት ግንበኞች ድንጋይ ጠራቢዎች አናጢዎች ወርቅ ሠሪዎች የጦር መሣሪያዎችና ሐኪሞች ለአፄ ልብነ ድንግል እንዲሰጥ ጠየቁ። አልቫሬዝና ጓደኞቹ 6 ዓመት ያህል በኢትዮጵያ ከተቀመጡ በኋላ ወደ አገራቸው ተመለሱ። ነገር ግን ጆን በርሙዴዝ የተባለው ፖርቹጋል ከአፄ ልብነ ድግንል ጋር ቀረ።

ከኢትዮጵያ ከወጡ ከሦስት ዓመታት በኋላ ወደ አገራቸው ገቡ። በመንገድ ላይ ብዙ ችግርና ድካም ደርሶባቸው ነበር። አልቫሬዝም አገሩ ሲገባ በኢትዮጵያ ያየውን ነገር ሁሉ ለንጉሡ ነገረው። በኢትዮጵያ የሚገኙትን ብዙ ቤተክርስቲያን ገዳሞች መነኲሰዎች ቄሶች በሠፊው አወራለት። የፖርቹጋልም ንጉሥ ንጉሥ ሚካኤል አፄ ልብነ ድንግል በላኩለት የውዳጅነት ደብዳቤ በጣም ተደሰተ። ከዚህ ወዲያ በፖርቹጋልና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ትልቅ ወዳጅንት ተፈጠረ። ከዚህ የተነሣ አፄ ልብነ ድንግል ከግራኝ መሐመድ ጋር ጦርነት ባደረጉበት ጊዜ የፖርቹጋል መንግሥት የጦር ዕርዳታ አድርጎላቸዋል።

ይህንንም በግራኝ መሐመድ ታሪክ ውስጥ በሠፊው እንማራለን። ከዚህም በላይ የፖርቹጋል መንግሥት ሚሲዮናውያንን በዚያን ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ላከ። እነርሱም ኢየሱሳውያን የተባሉ በካቶሊክ ሃይማኖት እንዲያምኑ ለማድረግ ነበር። ስለዚህ በ1549 ዓ.ም አቪዬዶ በተባለ ኢየሱሳዊ ሹምነት በኢትዮጵያ ውስጥ የፖርቹጋል መንግሥት ሚሲዮን ከፈተ።

ይህ የሆነው በአፄ ገላውዲዎስ ዘመነ መንግሥት ነው አቪዲዮ የኢየሱሳውያን ሚሲዮን ኃላፊ የነበረው አፄ ገላውዲዎስ የሮማን ካቶሊክ ሃይማኖት እንዲቀበሉ መጀመሪያ ሰበካቸው ሕዝቡም የካቶሊክ ሃይማኖት አምኖ እንዲቀበል እንዲያደርጉ አባበሏቸው። አቡን ደግሞ የሮማ እንዲያስመጡ ጠየቃቸው። የሮማ ጳጳስ በቤተ ክርስቲያን በኩል የበላይ አዛዥ መሆኑን እንዲያቁ አፄ ገላውዲዎስን መከራቸው። ዳሩ ግን ገላውዲዎስ ባለው በኦርቶዶክሳዊ ቤተ ክርስቲያን ጽኑ እምነት ስለነበራቸው የኦቪዩዶን ኀሳብ ሳይቀበሉት ቀሩ። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ብቻ የሚቀበሉ መሆናቸውን አስረዱት። የሮማ ጳጳስ በኢትዮጵያ ላይ ምንም የበላይነት እንደሌለው ነገሩት። ሆኖም ሚሲዮኑን በደስታ ተቀብለው ብዙ የደግነት ሥራ ይሠሩለት ነበር።

ከብዙ ዓመታት በኋላ ሌላ የኢየሱሳውያን ሚሲዮን የስፓኛ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ላከ። የዚህም ሚሲዮን መሪ ፒተር ፔዝ የተባለ የሰው መወደድ ያለው ሚሲዮናዊ ነበር። ይህ ሰው ከማንም ሰው ጋር በቀላሉ ለመላመድና ወዳጅነት ለማበጀት ትልቅ ስጦታ ነበረው። ከዚህም በላይ የቋንቋ ሰው ነበር። ስለዚህ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ግዕዝና አማርኛ በደንብ አጠናቆ ተማረ። ከዚህ በኋላ ትልቅ ትምህርት ቤት ከፈተ። ብዙ ሰዎች በተለይ ባላባት የሆኑት ልጆቻቸውን ወደዚህ ትምህርት ቤት ላኩ።

ፒተር ፔዝም የካቶሊክ ሃይማኖት እምነት በግዕዝ ተርጉሞት ስለ ነበር ተማሪዎቹን አስተምሮ ካቶሊክ አደረጋቸው።

ፔዝ በትግሬና በጉራጌ ትምህርት ቤቶች ከፍቶ ብዙ ተማሪዎች ካስተማረ በኋላ ተማሪዎቹ በየሥፍራቸው እየተዘዋወሩ የካቶሊክ ሃይማኖት እንዲያስተምሩ ላኳቸው በዚያ ዘመን የነበረው አፄ ሱስንዮስም የካቶሊክ ሃይማኖት ተቀበለ። ብዙዎችም የንጉሡ መኳንንት በዚህ አዲስ ሃይማኖት አመኑ። የካቶሊክ ሃይማኖት በግልጽ ለሕዝብ እንዲሰበክ ተደረገ። ንጉሡም የኦርቶዶክስ ቄሶች የቤተ ክርስቲያኑን ቅዳሴና ሥርዓት በሮማ ቤተ ክርስቲያን ደንብ እንዲያደርጉ አወጀ። ከዚህም በላይ አፄ ሱስንዮስ መላው ሕዝቡ እንደገና በካቶሊክ ሃይማኖት አምኖ እንዲጠመቅ አዘዙ።

ይህ የንጉሡ ትእዛዝ የካቶሊክ ሃይማኖት መስፋፋት ትልቅ ሁከት አስነሣ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኀላፊዎችና መላው በኦርቶዶክስ ሃይማኖት የሚያምነው ሕዝብ በንጉሡ ተነሡባቸው ብዙዎቹም መኳንንትና ባላባት አቡኑ ንጉሡን እንዲያወግዙ ጠቅዋቸው። በየጊዜው በዚህ አዲስ ሃይማኖት ምክንያት አገሩ ታወከ። ሰላም ፈጽሞ ጠፋ በመጨረሻ የርስ በርስ ውጊያ ተነሣ። በዚህ ጊዜ መካከል የካቶሊክ ሃይማኖት ችግር ምንም ውሳኔ ሳያገኝ ታሞ ሞተ።

ዙፋኑንም አፄ ፋሲል የተባለ ብልኅ ንጉሥ ወረሰ በካቶሊክ ሃይማኖት ምክንያት ብዙ ሁከት ደም መፋሰስ በግፍ ውስጥ መደረጉን ተገንዝበው። ስለዚህ የካቶሊክ ሚሲዮን ማስተማሩንና መስበኩን እንዲያቆም አስታወቀ። ሕዝቡም የካቶሊክን ሃይማኖት እንዳይቀበል አወጀ። ቄሶችም እንደዱሮው በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ደንብ እንዲያስተምሩና እንዲሰብኩ ሥልጣን ሰጣቸው።

ከዚህ በላይ አፄ ፋሲል ኢየሱሳውያን የሆኑትን ሁሉ ከኢትዮጵያ አወጥተዋቸው። በካቶሊክ ሃይማኖት ያመኑትን ኢትዮጵያውያን ደግሞ ንብረታቸውን ወርሰው አባረሩዋቸው። ከዚህ በኋላ በሃይማኖት በኩል ምንም ሁከት ሳያደርግ ሕዝቡ በሰላም ብዙ ዘመን ኖረ።

## ጥያቄዎች

1. ሜዲትራኒያን ባሕር የትኞችን ክፍለ ዓለሞች ይለያያል።
2. ኢትዮጵያ ከሠለጠኑት አገሮች በእንዴት ያሉ ምክንያቶች ተለይታ ነበር?
3. ተከታዮቹን ሐረጎች ወይም ቃላት አስረዳ፡-
   ሀ. የሜዲትራኒያን ዓለም
   ለ. አፍአዊ ታሪክ
4. ፖርቹጋሎች ወደ ኢትዮጵያ ስለምን መጡ?
5. ፖርቹጋሎች የሚያዋስንዋት ምን ምኖች ናቸው?

# ኢማም አህመድ ግራኝ

ባለፈው ምዕራፍ የፖርቹጋል ሚሲዮን በኢትዮጵያ እንዴት እንደተጀመረ ተምረናል። በዚህ ሚሲዮን አማካይነት በፖርቹጋልና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ትልቅ ወዳጅነት እንደተመሠረተ አይተናል።

በዚያን ጊዜ የፖርቹጋል መንግሥት ከቱርክ ጋር ሲዋጋ አፄ ልብነ ድንግል ፖርቹጋሎችን እንዲረዱ ተመልክተናል። ከዚህ የተነሣ አፄ ልብነ ድንግል ከግራኝ ኢማም አህመድ ጋር ሲዋጉ የፖርቹጋል መንግሥት መርዳቱን አውቀናል።

ኢማም አህመድ ግራኝ በ1510 ዓ.ም በሐረር ውስጥ ተነሥቶ በኃይሉ ትልቅ ሥልጣን ያገኘ ሰው ነበር። አህመድ ግራኝ ሐረርን ከያዘ በኋላ አዳልንና ዘይላን አስገብሮ ያዘ። ከዚህ በኋላ ግዛቱን በደቡብና በሰሜን ማስፋፋት ጀመረ። የግራኝ አህመድ ዋና ኅሳቡም ኢትዮጵያን በሙሉ ወር ሕዝቡን ለማስለም ነበር። እርሱም ከቱርክ መንግሥት ርዳታ ነበረው።

በዚያን ዘመን የቱርክ መንግሥት ግዛቱ በጣም ሰፊ ነበር። የቀይ ባሕር ዙርያ ጠረፍ ሁሉ በቱርክ ግዛት ውስጥ እንደ ነበር ታሪክ ይነግረናል። ሡልጣን ሳሊም የተባለው የቱርክ ንጉሥ ግብፅን ወሮ ነበር። ከዚህም በላይ የዐረቢያን የመሬት ሰላጤ የግብፅ ይዞታ ነበረች። ሡልጣን ሳሊም ኢትዮጵያን ወሮ የቱርክ ግዛት ለማድረግ ከፍ ያለ ምኞት ነበረው። ስለዚህ ሡልጣን ሳሊም አህመድ ግራኝን መሣሪያ አድርጎ ኢትዮጵያን ለመያዝ አሰበ። ከዚህም የተነሣ ሡልጣን ሳሊም ለግራኝ አህመድ የጦር መሣሪያና የሠለጠኑ የቱርክ ወታደሮች ላከለት።

መጀመሪያ እስላሞች ከመካ ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደስታ ተቀብሏቸው ነበር። ክርስቲያንም ሆነ እስላሙ ሃይማኖት በኩል ከዚህ በኋላ ምንም ልዩነት ሳያደርግ ብዙ ዘመን አንድ ላይ ኖረ።

በኋላ ግን የቱርክ እስላሞች በግራኝ አህመድ በኩል ኢትዮጵያን ለመውጋት ሲነሡ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዋጋት ግዴታ ሆነበት።

ኢማም አህመድ የቱርክ መንግሥት የሰጠውን የጦር መሣሪያና ወታደር በራሱ የጦር ኃይል ላይ ጨምሮ የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች ሊያጠፋ ተነሣ። በመጀመሪያ ጊዜ ያሰበው ሳይሆንለት ቀረ። ከሁለት ዓመታት በኋላ ግን የጦር ኃይሉን ጨምሮ እንደገና ተነሣ። እርሱም ከአፄ ልብነ ድንግል ጋር ተውግቶ ድል አደረገ። አፄ ልብነ ድንግልም ከጎንደር ሸሽተው ወደ መንዝ ገቡ። ከዚህ በኋላ የግራኝ አህመድ ጦር ክፍል ከኢትዮጵያ አብዛኛው ድል አድርጎ ያዘ። የግራኝ አህመድ ጦርም እስላም አልሆንም ያለውን ክርስቲያን ሁሉ ገደለው። ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችን ገዳሞችን አፈረሰ። ብዙ መጻሕፍት አቃጠለ።

አፄ ልብነ ድንግል የግራኝን ጦር ለመውጋት ወዳጃቸው የፖርቱጋል መንግሥት ርዳታ እንዲልክላቸው በርማዲዝ የተባለውን ፖርቱጋል ላኩት። እርሱም በመንገድ ብዙ ችግር ደርሶበት ከኢትዮጵያ በወጣ በሦስት ዓመቱ ፖርቱጋል ገባ።

የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤልም ስለ አፄ ድንግል ደኅንነት በሰማ ጊዜ በጣም ተደሰተ። ንጉሡም ወዲያውኑ አራት መቶ ወታደር ሄደው ለአፄ ልብነ ድንግል እንዲዋጉ አዘዘ። የዚህም ጦር አዛዥ የቫስኮ ደጋማን ልጅ ክሪስቶፈር ዳጋማን ሾሞ ላከው። ጦሩም መጥቶ ምጽዋ አጠገብ ሠፈረ።

ዳሩ ግን በዚያ ጊዜ የአፄ ልብነ ድንግል ጦር በጣም ደክሞ ነበር። ብዙዎቹ ደፋርና ታማኝ አሽከሮቻቸው አለቁ። ራሳቸውም አፄ ልብነ ድንግል በጠና ታመሙ በኋላም ከግራኝ ጦር ጋር የመጨረሻ ውጊያ በቤጌምድር አድርገው በደብረ ዳሞ ላይ ሞቱ።

ከዚህ በኋላ ንግሥቲቱ የፖርቱጋልን ጦር ይዛ ልጇን አፄ ገላውዴዎስን ልትገናኝ ወደ ደቡብ ሄዱ። በዚህን ጊዜ ግራኝ አህመድ ጣና ባሕር አጠገብ ነበር። ስለዚህ የፖርቱጋል ጦር ከአፄ ገላውዴዎስ ጋር እንዳይገናኝ በመንገድ ገጠመው። ሁለት ጊዜ ጦርነት ተደርጎ ማንኛውም ወገን ሳያሸንፍ ቀረ።

በዚህን ጊዜ ግራኝ የፖርቱጋልን ጦር እንደማያሸንፍ ተረዳና ከቱርክ መንግሥት ርዳታ መጠየቅ ግዴታ ሆነበት። ስለዚህ የጠቀየውን ርዳታ እንዲያገኝ ግራን ብዙ ገጸ በረከት ለቱርክ ንጉሥ ላከ። ባንድ ጦርነት ላይ

የማረከውን የአፄ ገላውዴዎስን ወንድም ለሡልጣኑ ስጦታ አበረከተ። ከዚህም የተነሣ የቱርክ ንጉሥ ዘጠኝ እምቶ ሰዎችና ብዙ የጦር መሣሪያ ለግራኝ ሰጠው።

ከዚህ በኋላ ግራኝ አህመድ በአዲስ ጉልበት ሆኖ ከፖርቹጋል ጋር ጦርነት ገጠመ። በዚህ ጦርነት ውስጥ ግማሹ የፖርቹጋል ወታደር ሞተ። የፖርቹጋል ጦር ኃላፊ ክርስቶፈር ዳጋማም ቆሰለ። በኋላም ተማርኮ በቱርኮች እጅ ሞተ። ከዚህም የተነሣ የተረፈው የፖርቹጋል ጦር ተስፋ ቆረጠ። ግራኝ ኃይሉን እደገና ድል አድራጊነትም እያገኘ ሄደ። የተረፉትንም የፖርቹጋል ወታደሮች ንቆ ተዋቸው። ከዚህም በላይ የቱርክ ወታደሮችን ላማካሪነት ካስቀራቸው በቀር ሁሉንም ወዳገራቸው እንዲመለሱ አሰናበተ።

ዳሩ ግን ንግሥቲቱ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የተረፉትን የፖርቹጋል ወታደሮች ይዘው ከልጃቸው ከአፄ ገላውዴዎስ ጋር ተደባለቁ። ከዚህ በኋላ አፄ ገላውዴዎስ ኃይለኛ ጦር ይዞ ግራኝ አህመድን ለመውጋት ዘመተ። ግራኝ አህመድ ግን ከፉኛ ድል ያደረገው ጠላት እንደገና ይነሣል ብሎ አላሰበም ነበር። ነገር ግን አፄ ገላውዴዎስ ደኅና የሠለጠነ ኃይለኛ ጦር ይዘው ግራኝን ሳያስበው ወረሩት። ሁለቱም ወገን በጣም ተዋጉ። በመጨረሻም ግራኝ በጦርነቱ ውስጥ ተውግቶ ሞተ። ወታደሮቹም ተበታተኑ። አፄ ገላውዴዎስም የግራኝን ጦር በሙሉ ድል አደረጉ።

ከዚህ ወዲያ አፄ ገላውዴዎስ በድል አድራጊነት ወዳባቶቻቸው ከተማ ወደ ጎንደር ተመለሱ። ያባታቸውን ወታደሮች ሁሉ ሰብስበው ደንበኛ የጦር ሠራዊት መሠረቱ። ግራኝ ያፈረሳቸውን ቤተ ክርስቲያኖችና ገዳሞች እንደገና ሠሩ። እንደዚህም ደግሞ በግራኝ ጊዜ የተቃጠሉትን መጻሕፍት ሁሉ እንደገና አጻፍዋቸው። ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ አዲስ የሰላምና የደስታ ዘመን ጀመረች።

## ጥያቄዎች

1. ስለ ግራኝ አህመድ ምን ሌላ ታሪክ ሰምተሃል?
2. የቱርክ መንግሥት ለምን ግራኝን ረዳ?
3. የፖርቹጋል መንግሥት ለምን ቱርኮችን ወጉ?

4. የፖርቹጋል ጦር አዛዥ ማን ነበር?
5. የቱርክ መንግሥት ምን ዓይነት ርዳታ ለግራኝ ሰጠ?

# አቡነ ተክለ ሃይማኖት

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በጣም የታወቁ ጻድቅ ሰው ነበሩ። በፊት ከነበሩት ጳጳሳት ስማቸውና ሥራቸው በታሪክ ጐልተው ይታያሉ። ተክለ ሃይማኖት በሸዋ ቡልጋ ውስጥ ተወለዱ። የተወለዱበት መንደር በተለይ ጽላልሽ ይባላል። እርሳቸው ከቤተ ክርስቲያን ሰዎች የአንድ ቄስ ልጅ ነበሩ። የአባታቸውም ስም ዘርዓ ዮሐንስ ይባላል። እናታቸውም ሣራ የምትባል ሴት ነበረች። ሁለቱም መካን ስለነበሩ ልጅ መውልደ ይናፍቃቸው ነበር። ከብዙ ዘመን በኋላ ግን ተክለ ሃይማኖትን ወለዱ። ልጃቸውም የተወለዱት በ1164 ዓ.ም ታኅሣሥ 24 ቀን እሑድ በሦስት ሰዓት ነው። ስማቸውንም ፍሥሐ ጽዮን ብለው አወጡላቸው። ትርጉሙ የጽዮን ደስታዋ ነው ማለት ነው። ዕድሜያቸውም ሰባት ዓመት ሲሞላ አባታቸው ፊደልን አስተማሯቸው። ከዚህ በኋላ ብሉይንና ሐዲስን በደረጃ አስጠንዋቸው። ይኸንም ተምረው ሲጨርሱ አሥራ ስድስት ዓመታቸው ነበር። በዚያን ጊዜ አባታቸው ወደ ጳጳሱ ወደ ጌርሎስ ወሰድዋቸው። በዚያም ዘመን የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አባ ብንያም ነበሩ። ፍሥሐ ጽዮንም ከጳጳሱ ዲቁና ተሹመው ወደ መኖሪያ ቦታቸው ከአባታቸው ጋር ተመለሱ። ግን ፍሥሐ ጽዮን በዕድሜ

ሲበስሉ ፈረስ መቀመጥ አውሬ ማደን በቀስት መንደፍና የጦር መሣሪያን ቅልጥፍና ዐወቁ። እርሳቸውም በሁለት ነገር በጣም ጎበዝ ወጣቸው። ፍሥሓ ጽዮን ኻያ ዓመት ሲሞላቸው እናትና አባታቸውን ከሀገር ሽማግሌዎች ያንዱን ልጅ አጩላቸው። ፍሥሐ ጽዮን ግን ሚስት ለማግባት አልፈቀዱም። ኑሯቸውን በሙሉ በድንግልና ለማሳለፍ ይፈልጉ ነበር። ነገር ግን ወላጆቻቸው በራሳቸው ሐሳብ ብቻ ልጃገረድዋን አመጡላቸው። እርሳቸውና ልጃገረድዋ የወንድና የሴት ጠባይ ሳይሠሩ ይኖሩ ጀመር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልጃገረድዋ ድንግል እንደሆነች ሞተች። ከዚህም የተነሣ ወጣቱ በድንግልናቸው ለመኖር ቻሉ ከዚህ በኋላ ወደ ጳጳጹ ወደ ጌርሎስ ሄዱ። በዚያን ጊዜ ጳጳሱ ቅስና ሰጥተው በሽዋ አውራጃ ሀሉ ሊቀ ካህናት ሾሟቸው። ስለዚህ ወንጌልን በሰፊው ለሕዝቡ ማስተማር ጀመሩ። ደግሞ በክርስቶስ አምነው ያልተጠመቁትን አረማውያን ማጥመቅ የክህነታቸው ሥራ ሆኖ። በዚያን ዘመን ብዙ ሟርተኞች ጠንቋዮች በኢትዮጵያ ውስጥ ነበሩ። ነገር ግን ፍሥሐ ጽዮን የጣዖት አምልኮት ውሸት ነገር መሆኑን ከወንጌል እየጠቀሱ አስተማሩ። መተሎሜ የተባለውንም ንጉሥ ወንጌል አስተምረው በክርስቶስ አሳመኑት። ንጉሡም የጣዖት ቤቶች ህሉ እንዲፈርሱ አደረገ። ደግሞ ከላይ ቅቤ እየቀቡ ከሥሩ ጨሌ እየጣሉ አምላካችን የሚሉትን ዛፍ አስቆረጠው። ፍሥሐ ጽዮን ሕዝቡ በአንድ እግዚአብሔር ብቻ እንዲያምኑ ሰበኩ። ስለዚህ በአድባር በአውገር በዛር በመናፍስት ማምለክ በሕዝቡ ዘንድ መቅረት ጀመረ። ከዚህም የተነሣ በፍሥሐ ጽዮን ፋንታ ተክለ ሃይማኖት ተባሉ። ትርጉሙ የሃይማኖት ምሰሶ ማለት ነው። በዚያን ጊዜ በሽዋ የምንኩስና ትምህርት የለም ነበር። ስለዚህ የምንኩስናን ትምርህት ለመማር ወደገሼ መሄድ ግድ ሆነባቸው። እዚያም ከአባ ጸሎተ ሚካኤል ጋር አሥር ዓመታት ተቀመጡ። የመነኩሳትንም ሕግ አጠኑ። ከዚህ በኋላ ወሎ ሐይቅ ከሚባለው ገዳም አሥር ዓመታት ኖሩ። ከዚያም በአባ ኢየሱስ ሞዓ እጅ በአንጦንስ ሕግ መነኰሱ ይህን ገዳም ለቀው በትግሬ ደብረ ዳሞ በሚባለው ገዳም አሥራ ሁለት ዓመት ኖሩ። ግን የደብረ ዳሞን ገዳም ለማየት አስቸጋሪ ነው።

አንድ ስው ገዳሙን ለማየት ሲፈልግ በጠንካራ ገመድ ወገቡን ታስሮ ገደሉን ለመውጣት ከላይ መጐተት አለበት። እንደዚሁም አቡነ ተክለ

ሃይማኖት ወገባቸውን ታስረው ሲጎተቱ ገመዱ ተበጠሰባቸው። ሆኖም ስድስት ክንፎች አብቅለው እንደ ወፍ በረሩ ሲል ገድላቸው ይናገራል። ተክለ ሃይማኖት በትግረ የቅዱሳንን ገዳማትና የመነኰሳትንም ቦታ ሁሉ እንደ ጎበኙ የታመነ ነው። በኋላም ኢየሩሳሌም ሄደው ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት መስቀል ሳሙ። ኢየሩሳሌም ሳሉ ጌታችን ተአምራት የሠራባቸውን ቦታዎች ሁሉ ጎበኙ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ሸዋ ተመልሰው በወገዳ በአንድ ጫካ በምናኔ ለመኖር ሞከሩ። ከዚህም ወጥተው ግራርያ በምትባለው ሀገር በአንድ ዋሻ ውስጥ ገቡ። ከውስጡም ስለታም ጦሮች ሁለቱን በፊታቸው ሁለቱን በኋላቸው ሁለቱን በቀኛቸው ሁለቱን በግራቸው እንደሚጠቀሟቸው አድርገው ተከሏቸው ይባላል።

በዚያን ጊዜ መንግሥት የዛጓ ወገኖች ነበረ። እነርሱም መንግሥትን ከወረሱት ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት ዓመታት ነበራቸው። ዳሩ ግን 1253 ዓ.ም መንግሥት ከእስራኤል ወገን ለሆነው ለይኩኖ አምላክ ተመለሰ። በዚያን ጊዜ ወንጌልን ከሚያስተምሩ ሰዎች ክብርና ዝና ያላቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖት ነበሩ። ስለዚህ በሚገባ ሥርዓተ ጸሎት አድርሰው ንጉሡን ይኩኖ አምላክን ቅብዓ መንግሥት ቀቡት። ንጉሡም ከመንግሥቱ ሢሶውን ሰጥቶ በደብረ ሊባኖስ አጨጌነት ሾማቸው።

በሹመታቸውም ብዙ ጊዜ ሡሩበት ከቤተ ክርስቲያናት አስተዳደርና ከጸሎት ተጋድሏቸው ጽናት የተነሣ አንዲት እግራቸው ተሰበረች። ስባሪዋንም ተማሪዎቻቸው በጨርቅ ጠቅልለው በደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን ከመንበሩ እግር በታች ቀበሯት ይባላል። በኋላም ባንዲቱ እግራቸው ሰባት ዓመታት ቆመው ጸለዩ ሲል ገድላቸው ይተርካል። በመጨረሻ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በ1263 ዓ.ም አረፉ።

# ጥያቄዎች

1. ተከታዮቹን ቃላት ፍታ።
   ሀ. ምንኩስናለ. ዲቁና
   ሐ. ቅስና   መ. ምናኔ

2. አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ክርስቲያናዊ ትምህርት በመጠኑ ጻፍ።
3. የዱሮው የኢትዮጵያ ስፖርት እንዴት ያለ ነበር?
4. የድሮውንና የአሁኑ የጋብቻ ሥርዓት አወዳድር።
5. አቡነ ተክለ ሃይማኖት የእጨጌነት ማዕርግ በምን ምክንያት አገኙት?

# ጎንደር

ባለ ታሪክ ከሆኑት ጥንታውያን የኢትዮጵያ መናገሻ ከተሞች አንዱ ጎንደር ነው። አፄ ፋሲል በ1624 ዓ.ም ጎንደር የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ እንዲሆን ቆረቆሩት። አፄ ፋሲል አባታቸው የተቀበሉትን የካቶሊክን ሃይማኖት ትተው በጥንቱ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት አምነው የኢየሱሳውያንን ሚሲዮን ከኢትዮጵያ ካስወጡ በኋላ መናገሻ ከተማቸውን ከላስታ ነቅለው ጎንደር ተከሉ። ጎንደር ብዙ ጥንታውያን ቤተ ክርስቲያናት ገዳማት ትላልቅ የግንብ ቤቶችና ቤተ መንግሥቶች ይገኙበታል። ኢትዮጵያ በአግዓዚያን ማለት ነፃ አውጭዎች ማለት ነው። ይኸውም የሆነው ከግራኝ ወረራ በኋላ ነው።

ጎንደር በመንፈሳዊ ትምህርት በኩል የታወቀ ጥንታዊ ከተማ ነበር። ቅኔና ዜማ እንደዚሁም በጠቅላላው የቤተ ክህነት ትምህርት የሚያስተምሩ ብዙ ገዳሞችና ቤተ ክርስቲያናት ነበሩ። በመንፈሳዊ በኩል ከፍ ያለ ትምህርት ለማግኘት የሚፈልጉ ተማሪዎች ከሸዋ ከጎጃምና ከትግሬ ወደ ጎንደር ይሄዱ ነበር። ጎንደር የቅኔ ከተማ እየተባለ እስካሁን ድረስ ይነሣል። በኋላ ግን በደርቡሾችና በኢጣልያ ወረራ ዘመን ብዙ ገዳሞችና ቤተ

ክርስቲያናት ፈረሱ። ብዙ መጻሕፍት ተቃጠሉ። ብዙ የዜማና የቅኔ መምህራን ተገደሉ።

ጥንታዊው ጎንደር ብዙ ዘመናት ሙሉ የነገሥታት ከተማ ሆኖ ኖረ። በከተማው ውስጥም በየጊዜው የተነሡትን የጎንደር ንጉሦች የግንብ ምሽጎች ታላላቅ ቤተ መንግሥቶችና ቤተ ክርስቲያናት አሠሩ። ጎንደር ከፍ ካለ ቦታ ላይ የተቆረቆረ ሲሆን የከተማው ዙሪያ በግንብ የተከበበ ነው። የጥንቱ ንጉሣዊ ከተማ አሥራ ሁለት የታወቁ በሮች አሉት። ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የራስ በር የአዛዥ በርና የዳኞች በር ናቸው።

በጎንደር ከተማ ውስጥ ከሚታዩት ታላላቅ ምሽጎችና ቤተ መንግሥቶች ትልቁና ስመጥሩው የፋሲል ግንብ የተባለው ቤት ነው። ይህ ግንብ የተሠራው በአሥራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን በየጊዜው በተደረገው ጦርነት ሳይፈርስ እስከዛሬ ድረስ ቆሞ ይታያል። አፄ ፋሲል ከሠሩአቸው የግንብ ቤቶች ውስጥ ፍቅረ ግንብ የሚባለው ቤተ መጻሕፍት የነበረውና የአንበሳ ቤቱን ለማየት ይቻላል። የራስ በር የተባለው አጠገብ የፈረሰኞች አዛዥ ይቀመጥበት የነበረው ግንብ ቤት እስከዛሬ አለ።

የጎንደር የግንብ ቤቶች እንደጥንታዊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሮቹና መስኮቶቹ የቀስት ዓይነት መልክ አላቸው። ዙሪያውን የግንቡ ጫፍ መስኮት ዓይነት ቅርጽ አለው። ውስጡም ሰፋፊ አዳራሾች አሉት። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ፍርድ የሚሰጥበት ችሎት ነው።

ከዚህም በላይ ስመጥሩው የአፄ ዓለም ሰገድ ግንብ በዚሁ በታሪካዊው ጎንደር ከተማ ውስጥ ይገኛል። ከአፄ ዓለም ሰገድ ቤተ መንግሥትም አጠገብ የንግሥት ምንትዋብ ቤተ መንግሥት ቆሟል። ይህ ውብ ቤተ መንግሥት ባለ ሁለት ሰገነት ሲሆን ሦስት ታላላቅ የመስታወት በሮች አሉት።

በጣም ከታወቁት የጎንደር ግንቦች ውስጥ የቀሩት ደግሞ ኢያሱ ብርሃን ቤተ መንግሥት የፈረሰው ቍስቋም ቤተ መንግሥትና ራስ ሚካኤል ምሽጎች ናቸው።

በጎንደር ከተማ ውስጥ በጣም የሠለጠኑ ልዩ ልዩ ሸማኔዎች ቆዳ ፋቂዎች ብረት ቀጥቃጮች ቀለም ቀቢዎች አናጢዎች ግንበኞች ብር

አፍሳሺዎች ወርቅ ሠሪዎች እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮችን የሚሠሩ አያሌ ባለሙያዎች ነበሩ። ሸማኔዎቹ ከጥጥና ከበግ ጸጉር ሸማ እየሠሩ ሕዝቡን ያለብሱ ነበር። ብረት ቀጥቃጮችና ብር አፍሳሾችም ልዩ ልዩ የቤትና የቤተ ክርስቲያን ዕቃ ይሠሩ ነበር። አብዛኛው የቀረው የጎንደር ሕዝብ ሥራ ቤተ ክህነትን ማገልገል ነበር። በጥንት ጊዜ ጎንደር የመንፈሳዊ ትምህርት የሚገኝበት ከተማ ብቻ ሳይሆን የንግድ የጥበብ የነጋዴዎችና የባለሙያዎች አገር እንደ ነበር ታሪኩ ይመሰክራል።

ጎንደር ሦስት መቶ ዓመታት ሙሉ የጥበብና የሰላም ጊዜ አሳለፈ። ከዚህ በኋላ ግን ቀስ በቀስ እየተዳከመ ሄደ። በመጨረሻም በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የጎንደር ዘመን አልቆ ወደ ሸዋ ተዛወረ።

# ጥያቄዎች

1. የአግዓዝያንን ትርጉም መጥነህ አስረዳ።
2. ጎንደር የቅኔ ከተማ እየተባለ የሚነሣው ስለምንድር ነው?
3. ድርቡሾች ወደ ጎንደር መጠው ምን ምኖችን አጠፉ?
4. ጎንደርንና ደሴን አወዳድራቸው።
5. የድሮውን እይንግድ ሁናቴ በመጠኑ ጻፍ።
6. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አስረዳ፦
   ሀ. ጎንደር ሦስት መቶ ዓመታት ሙሉ የጥበብና የሰላም ጊዜ አሳለፈ።
   ለ. ከነዚህም ውስጥ አንዱ ፍርድ የሚሰጥበት ችሎት ነበር።

# አፄ ቴዎድሮስ

ከዚህ በፊት ያነበብነው ከቀዳማዊ ምኒልክ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የነገሥታት ታሪክ ነው። እነዚም ነገሥታት የሰሎሞን ዘር መሆናቸውን ተምረናል።

በዚያ ዘመን ኢትዮጵያ ተከፋፍላ በመሳፍንት በመገዛትዋ በመሳፍንቱ መካከል በየጊዜው ጦርነት ይደረግ ነበር። ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች እየሸፈቱ ንጉሥ ለመሆን በብዙ ይደክሙ ነበር። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ልጅ ካሣ ነበሩ። አባታቸው የታውቁ ባላባት ደጃዝማች ኃይሉ ሲሆኑ እናታቸው ደግሞ አንዲት ተራ የቋራ ተወላጅ ሴት ነበሩ። ልጅ ካሣ በ1811 ዓ.ም በቋራ ተወለዱ። ገና በልጅነታቸው አባታቸው ስለሞቱ እናታቸው ኮሶ እየሸጡ እንዳሳደጉዋቸው ይነገራል። በኋላ ግን አጎታቸው ደጃዝማች ክንፉ ደግ ሰው ስለነበሩ ከናታቸው ወስደው ሊያስተምሩዋችው ፈለጉ። በዚያን ጊዜ በጣና ባሕር አጠገብ የነበረው ገዳም በመንፈሳዊና በግብረ ገብነት ትምህርት የታወቀ ነበር። ስለዚህ ደጃዝማች ክንፉ ልጅ ካሣን ወደዚህ ገዳም ወስደው አስገቡዋቸው።

ልጅ ካሣም የገዳሙን ትምህርት በደንብ አጠናቀው ተማሩ። በጥቂት ጊዜ ውስጥም በጣም የተመሰገኑ ተማሪ ወጣቸው። ትምህርት የሚገባቸውና አስትዋይ ተማሪ ነበሩ። ከሌላው የመንፈሳዊ ትምህርታቸው ባላይ የዳዊትን መዝሙርና ምስጋና በቃላቸው አጠኑ። የልጅ ካሣ የትምህርት ፍላጎት በመንፈሳዊ ትምህርት ብቻ አልተወሰነም። በጠቅላላው በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የሚደሰቱ ነበሩ። ስለዚህ በገዳም ሳሉ ብዙ መጻሕፍትና የእጅ ጽሑፎች ሰብሰቡ።

ከዚህም የተነሣ ሥልጣን ካገኙ በኋላ በመቅደላ አንድ ቤተ መጻሕፍት ሊያቋቁሙ ቻሉ። በኋላ ግን እንግሊዞች መጻሕፍቱን ሁሉ ዘርፈው ወስድዋቸዋል።

ዛሬ እነዚህን መጻሕፍት በለንደን የጥንት ሥራዎች በሚቀመጡበትና በሚታዩበት ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ለማይት ይቻላል።

ልጅ ካሣ የቤተ ክህነት ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ወዳ አጎታቸው ዘንድ ተመለሱ። በአጎታቸውም ቤት ብዙ ጊዜ ተቀመጡ። ካሣ ከልጅነታቸው ጀምርው ነቃ ያሉና ጎበዝ ነበሩ። በማንኛውም ነገር የበላይ ለመሆንና በፈረስም እሽቅድድም መሪ ለመሆን ከፍ ያለ ምኞት ነበራቸው። ስለ ጦርም ትምህርት በደንብ አጠናቀው ተማሩ። ጋሻና ጦር በጣም ይወዱ ነበር። ስለዚህ አወራወርና የጋሻ አመካከት ልምምድ ሁል ጊዜ ያደርጉ ነበር። በአጎታቸውም ቤት ሆነው ጥሩ ፈረሰኛ ወጣቸው።

ልጅ ካሣ ነፍስ ሲያውቁ ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ለመግዛት የጋለ ፍላጎት አደረባቸው። ፍላጎታቸውንም ከፍጻሜ ለማድረስ ብዙ ሰዎች ማግኘት ግዴታ ሆነባቸው። ስለዚህ በ1842 ዓ.ም ወታደር የሚሆንዋቸው ብዙ ጎበዝ ሰዎች ሰበሰቡ። ከነዚህም ውጥ ጥቂቶቹ አብሮ አደጎቻቸው ነበሩ።

ከዚህ በፊት እንዳነበብነው አገራችን ኢትዮጵያ ተከፋፍላ በልዩ ልዩ መሳፍንት ትገዛ ነበር። ስለዚህ ልጅ ካሳ አንድ ለማድረግ ሲነሡ በወዳጅነትም ሆነ በፍርኀት ብዙ የሚረድዋቸው ሰዎች አገኙ። በአጭር ጊዜም ውስጥ የቋራ ገዥ ለመሆን ቻሉ። ከዚህም በኋላ ራሳቸውን ደጃዝማች ካሣ ብለው ሾሙ። ስማቸው ሲነሣ በሕዝብ ዘንድ ፍርሃትና ሽብር ይሆን ነበር። የልጅ ካሣ ስም ሲጠራ ሽፍታውና ዐባይ ገነኑ ሁሉ ይሸበር ነበር። ልጅ ካሣ መጀመሪያ ደጃች ወንድይራድ ወግተው አፈር አስጋጡት። ቀጥሎም ደጃች ጎሹንና ራስ ዓሊን ድል አደረጉ። ከዚህ በኋላ ስማቸው በጣም የተከበረና የገነነ ሆነ። በድል ድልድዮችም ላይ እየተሸጋገረ ኃይላቸው ጉብዝናቸውና የጦር ጥበባቸው በመላ ኢትዮጵያ ታወቀ ተዝናና።

የራስ ዓሊን ዘርፎችና ራሳቸውን ራስ ዓሊን ድል ካደረጉ በኋላ ከሦስተኛው ዮሐንስ ጋር ተዋግተው ድል ነሡና ጎንደርን ያዙ። የአገዛዙንም ሥርዓት አሻሽለው ጥቂት ቀና ከመሩት በኋላ ለእንደራሴያቸው ጥበቃውን ሰጥተው ወደ ሰሜን ገሠገሡ። በዚያም ደጃች ውቤን አሸንፈው በአቡነ ሰላማ እጅ ተቀብተው በ1847 ዓ.ም የካቲት 5 ቀን የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ተቀዳጁ። በዚህም ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ የ37 ዓመት ጎልማሳ ነበሩ።

ከዚህም በኋላ ኃይለኛ ጦር ይዘው ወሎንና ሸዋን ለማስገበር ይዘምቱ ዘንድ ታላቅ ዝግጅት አደረጉ። ነገር ግን ወታደሮቻቸው በአልፉት ጦርነቶ ደክሟቸው ነበር። ስለዚህ አንዳንድ መሰል ደፋሮች አሽከሮቻቸው ጥቂት ቀናት እንዲያርፉ ጠየቋቸው። አፄ ቴዎድሮስ ግን ምኞታቸው በጣም የተነሣሣ ስለ ነበር ኢትዮጵያ አንድ ከማድረጋቸው በፊት ማንም ሰው ዕረፍት እንደማያስፈልገው ተናግረው እንደገና መንፈሳቸውን በትኩስ መንፈስ ቀሰቀሱላቸው።

በዚያን ጊዜ ወሎ በወይዘሮ ወርቂት ግዛት ነበር። ንጉሥ ኃይለ መለኮት አፄ ቴዎድሮስ ወሎንና ሸዋን ለመውጋት እንደተነሡ በሰሙ ጊዜ ከወይዘሮ ወርቂት ጋር ሆነው ቴዎድሮስ በክቶ ለመመለስ ተስማሙ። ነገር ግን ያለ ዕድል አይሆንምና ንጉሥ ኃይለ መለኮት በድንገት ታመው ሞቱ።

አፄ ቴዎድሮስ በእቅዳቸው መሠረት አስቀድመው ወሎን ድል አደረጉና ወደ ሸዋ ተሻገሩ። ወደ ሸዋም ሲገቡ መክቶ ሊያግዳቸው የቻለ ጦር አልተገኘም። ስለዚህ ድል አድርገው ከግባቸው ለመድረስና የአዲስ አመራር ደንባቸውን ለማከናወን ቻሉ። አፄ ቴዎድሮስ ወሎንና ሸዋን ካስገበሩ በኋላ ዋና ዋና ባላባቶችን እየሾሙ አስደሰቱት። የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ልጅ ምኒልክን ግን እያስተማሩ ለማሳደግ ወደ ጎንደር ይዘዋቸው ሲመለሱ ጎንደር አሸበራርቃ በክብርና በደስታ ተቀበለቻቸው። ይሁንና ምንም አፄ ቴዎድሮስ ጎጃምን ቤገምድርን ትግሬን ወሎንና ሸዋን ይዘው ቢያዋሕዱም ምኞታቸው በዚህ ብቻ ተወስኖ የኢትዮጵያን ጠረፎች የማስፋፋት ሐሳባቸው ሳይበርድ ያስተዳድሩ እንደነበረ ይነገራል።

አፄ ቴዎድሮስ ቀጥለው ቤተ ክህነትን ሊያሻሽሏትና ሕግን ሊያወጡላት ተነሡ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ባንድ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት እንዲያምን ለማድረግ ቆረጡ። ከዚህም የተነሣ ሃይማኖት ያልተቀበለው ሁሉ ይቀጡት ነበር።

እንደዚህም ደግሞ አንድ ወንድ ባንድ ሚስት ብቻ እንዲረጋ አወጁ። ስለዚህ አፄ ቴዎድሮስ ለሕዝባቸው መልካም አርአያ ለመሆን ዕቁባታቸውን ሁሉ ትተው የቀረውን ሕይወታቸውን በሙሉ ካንድ ሚስታቸው ከእቴጌ ተዋበች ጋር አሳለፉ።

ከዚህ ቀጥለው አፄ ቴዎድሮስ ሕዝባቸው ባንድ ቦታ ረግቶ ትጉ ሠራተኛ ሆኖ እንዲቀመጥ አደረጉ። እያንዳዱም ሰው በያዘው ሥራ እንዲረጋ አወጁ። ገበሬዎችንም በብዙ እህል እንዲያመርቱ አበረታትትዋቸዋል። እንደዚሁም ደግሞ ነጋዴዎች ሁሉ በደንብ እንዲነግዱና ለሕዝቡ እንዲሸጡ አደረጉ። ነጋዴዎችና መንገደኞች እንደልባቸው እንዲዛወሩ አፄ ቴዎድሮስ ሽፍቶችንና ወንበዴዎችን አጠፉ።

አፄ ቴዎድሮስ ስለ ኢትዮጵያ ልማትና እድገት የነበራቸው ኅሳብ ኢትዮጵያን በማቅናትና አንድ በማድረግ ብቻ አልተወሰነም። ከአውሮፓ አገሮችም ጋር ግንኙነት በማድረግ ኢትዮጵያን ለማሠልጠን ያጋለ ምኞት ነበራቸው። ስለዚህ ስለዚህ ለእንሊዝ ንግሥት ለቪክቶሪያን ለፈረንሳይ ንጉሥ ለናፖሊዮን ደብዳቤ ጽፈው ላኩ። አፄ ቴዎድሮስ በደብዳቤአቸው ውስጥ ለሁለቱም አገሮች አምባሳሸር ለመላክ እንደፈለጉ ገለጹ። ከዚህ በላይ ደብዳቤ ይዞ በሄደው ሰው እጅ መልስ እንዲላክላቸው ጠየቁ።

ጻፉ ግን አፄ ቴዎድሮስ ለጻፉት ደብዳቤ ምንም መልስ ሳያገኙ ቀሩ። አፄ ቴዎድሮስ ለጻፉት ደብዳቤ መልስ ባለማግኘታቸው ክብራቸው እንደ ተነካና እንደተሰደቡ ቆጠሩት። በዚህም ጉዳይ በጣን ተናደው ስለነበር በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ከነበሩት የእንግሊዝ ተወላጆች ውስጥ ጥቂቶቹን አሰርዋቸው። ንግሥት ቪክቶሪያም ዜጎችዋ በመታሰራቸው በሰማች ጊዜ የታሰሩትን እንዲፈቱ ለአፄ ቴዎድሮስ ላከች።

አፄ ቴዎድሮስ ግን ደብዳቤዋን ቸላ አሉት። ስለዚህ የእንግሊዝ መንግሥት እስረኞቹን ለማስፈታትና አፄ ቴዎድሮስን ለመያዝ ወደ ኢትዮጵያ ጦር ላከ። የእንግሊዝ ጦር በቀላሉ ድል የሚነሡበትንና አፄ ቴዎድሮስን በሕይወታቸው የሚማረኩበትን ዘዴ አጠና። መጀመሪያ ከትግሬው ባላባት ከደጃዝማች ካሣና ከአፄ ቴዎድሮስ ጠላቶች ጋር የእንግሊዝ ጦር ተወዳጀ። እነሱም የአፄ ቴዎድሮስ ጦር ድል የሚሆንበትን መንገድ ለጠላት ጦር አስረዱ። ከዚህም የተነሣ በ1860 ዓ.ም በጦር አዝማቻቸው በፊታውራሪ ገብርዬ የተመራው ዋናው የአፄ ቴዎድሮስ ጦር ድል ሆነ። ደፋርና ታማኝ አሽከሮቻቸው ተራ በተራ አለቁ። አፄ ቴዎድሮስ ድል መሆናቸውን ሲረዱ የተረፉትን አሽከሮቻቸው ከአደጋው ሸሽው እንዲያመልጡ አሰናበትዋቸው። እርሳቸውም በቆራጥነት መንፈስ ምን

ማድረግ እንደሚሻል ሲያወጡና ሲያወርዱ የእንግሊዝ ጦር አለቃ /መሪ/ አፄ ቴዎድሮስ እጃቸውን እንዲሰጡ ላከባቸው። እርሳቸውም እጃቸውን እንዳይሰጡ መለሱለት። ከዚህም በኋላ የአሽከራቸውን የገብርዬን ሞት እያሰላደሉ «እኔ ቴዎድሮስ እንጂ ለጠላት አሳልፌ ከምስጥ ራሴን በራሴ ድል ማድረግ እወዳለሁ» ሲሉ ተናግረው ሽጉጣቸውን ጠጥተው አረፉ።

የአፄ ቴዎድሮስም ሞት በተሰማ ጊዜ በመላ ኢትዮጵያ ትልቅ ድንጋጤና ሐዘን ሆነ። ኢትዮጵያ ትልቅ ኀሳበ ሰፊ ሰው እንደተለያት ተሰማት። ወዳጆቻቸውና አሽከሮቻቸው ጠላቶቻቸው ሁሉ ሳይቀሩ የደም እንባ አለቀሱ።

ዛሬ አፄ ቴዎድሮስ በመላ ኢትዮጵያ በጉብዝናቸና በአርበኝነት ሥራቸው ዘወትር ይነሣሉ። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ በአንድ ንጉሠ ነገሥት ሥር እንድትተዳደር ለመጀመሪያ ጊዜ ያሰቡ ሰው ስለሆኑ ታሪካቸው ዘላለም ይኖራል። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ጎጃምን ቤጌምድርን ስሜንን ትግሬን ወሎንና ሸዋን አንድ ማድረጋቸው ኀሳባቸው ትልቅ መሆኑን ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ በአውሮፓና በዓለም ዳግመኛ እንድትታወቅ ያደረጉ አፄ ቴዎድሮስ በመሆናቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አይረሳም።

## ጥያቄዎች

1. አፄ ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው በፊት የኢትዮጵያ አገዛዝ እንዴት ነበር?
2. የአፄ ቴዎድሮስ ትውልድ እንዴት ነው?
3. አፄ ቴዎድሮስ ምን ዓይነት ኀሳብና ጠባይ ነበራቸው?
4. አፄ ቴዎድሮስ እነማንን ድል አደረጉ?
5. አፄ ቴዎድሮስ ድል ለምን ሆኑ?
6. አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን በመግደላቸው ጥሩ ሠሩ ወይስ አልሠሩም?

# አፄ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስመጥር ከሆኑት ጠቅላይ ግዛቶች አንዱ ትግሬ ነው። በትግሬ በተለይ በአኩስም ስለሆነ ነው ታሪክ ከዚህ በፊት በሰፊው ተምረናል። አሁን በትግሬ ስለተነሡ ስለ አፄ ዮሐንስ ታሪክ እንማራለን።

አፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ድል ከሆኑ በኋላ እንግሊዞች የሸዋን የጎንደርን የትግሬን መኳንንት ነፃ ለቀቅዋቸው። ከዚህ ወዲያ ብዙ ዓመታት ተረስቶ የነበርው የርስ በርስ ውጊያ እንደ ገና ተጀመረ። የሸዋ የትግሬና የጎንደርን ንጉሥ ሁሉ በበኩሉ እንደ አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ለመግዛት ኃይለኛ ሰዎች አንዱ በጎንደር የነገሡት አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ነበሩ። አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ከብዙ ውጊያ በኋላ ሦስት ዓመታት ሙሉ ነግሠው ገዙ። ነገር ግን ለመንግሥት ትልቅ ፍላጎት የነበራቸው ደጃዝማች በዝብዝ ካሣ የሚባሉ ሌላ ሰው ነበሩ። ዳሩ ግን አፄ ቴዎድሮስን ከከዱ ሰዎች ጋር አንድ ላይ ሆነው እንግሊዞች ድል እንዲያደርጉ ረዱ። አፄ ቴዎድሮስ ድል ከሆኑ በኋላ ደጃዝማች በዝብዝ ካሣ ዙፋኑን ለመውረስ ፈለጉ። ስለዚህ ደጃዝማች በዝብዝ ካሣ አፄ ተክለ ጊዮርጊስን ከዙፋን አውርደው ሊነግሡ ተነሡ ደጃዝማች ካሣም በብዙ ጦር ተወዳዳሪዎቻቸውን ሁሉ አንድ ባንድ ድል ነሥተው በመጨረሻ አፄ ተክለ ጊዮርጊስን እንግሊዝ በሰጣቸው መሣሪያዎች ድል አደረጉ። ከጊዝህ በኋላ የንጉሦች ንጉሥ መሆናቸውን አወጁ። የዙፋን ስማቸውንም ዮሐንስ አራተኛ ብለው በ1876 ዓ.ም በአኩስም ከተማ ዘውድ ደፉ።

አፄ ዮሐንስ በጣም ኀበዝና ሃይማኖተኛ ንጉሥ ነበሩ። በርሳቸው የሚመራ ኃይለኛ የጦር ሠራዊት አቋቋሙ። የአፄ ዮሐንስ ዋና ኀሳብ የኢትዮጵያን ሃይማኖት አንድ ለማድረግ ነበር። ስለዚህ በኢትዮጵያ የነበሩትን ሚሲዮናውያን ሁሉ ከአገር አስወጡ ኢትዮጵያ የራሷ ሃይማኖት መምህራን ያላት አገር መሆኗን አስረዱ።

አፄ ዮሐንስ የውጭ አገር ሚሲዮናውያንን ካስወጡ በኋላ ከግብፅ አገር የወንጌል መምህራን አስመጥተው በኢትዮጵያ ውስጥ ክርስቲያን ያልሆኑትን አስበኩ። የክርስቲያንንም ሃይማኖት አምኖ ያልተቀበለው ሁሉ

ትልቅ ሥቃይና መከራ ያሳዩት ነበር። አፄ ዮሐንስ በጣም ሃይማኖተኛ ስለ ነበሩ ትምባሆ የሚያጨስና የሚጎርስ ሰው ባዩን በሰሙ ጊዜ ይቀጡት እንደ ነበር ይነገራል።

አፄ ዮሐንስ በነገሡበት ዘመን የነበረው የግብፅ ንጉሥ በጣም ኃይለኛ ንጉሥና ግዛቱንም ለማስፋፋት የጋለ ፍላጎት ያለው ሰው ነበር። ስለዚህ ኢትዮጵያን ሊወር ጦሩን ይዞ ተነሣ። ኢትዮጵያንም በቀላሉ ድል አድርጎ ለመያዝ ትልቅ ተስፋ ነበረው። አፄ ዮሐንስም የግብፅን ጉራ ሲሰሙ በጣም ተናደዱ። ሙሉ ጦራቸውን ይዘው ለጦርነት ተሰለፉ። የግብፅም ወታደር ወደ ኢትዮጵያ ሲጓዝ የአፄ ዮሐንስ ጦር ካራ ላይ ገጥሞት ድል አደረገው። በዚህ ጦርነት ውስጥ ከግማሽ የሚበልጠው የጠላት ጦር አለቀ። ከኢትዮጵያውያን ወገን ግን የሞቱት ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። ከዚህም በላይ የአፄ ዮሐንስ ጦር ብዙ ጠመንጃና መሣሪያ ገፈፈ። ብዙ ግብፆችም ማረከ።

ኢትዮጵያ የምትፈልገው የጅ ጥበብን የሚያስተምሩ መምህራን ብቻ መሆኑን ገለጹ። ሃይማኖት ከሚያስተምሩ ሰዎች ይልቅ የሸማ ምንጣፍ የፋኖስ የምስማር አሠራር የሚያስተምሩ መምህራንን እንዲወስዱ አስረዱ። ስለዚህ የሚስዮናውያኑን ወደ ሌላ ክፍለ ዓለም ሄደው ክርስቲያን ያልሆኑትን አገሮች እንዲያስተምሩ አሰናበትዋቸው።

እንደዚሁም ደግሞ አፄ ዮሐንስ ሥልጣኑን በያዙበት ዘመን በሱዳን ውስጥ በጣም ጠንካራ እስላሞች የሆኑ ደርቡሾች የሚባሉ ነበሩ። የነሱም ዋና ዓላማ የእስላም ሃይማኖት ለማስፋፋት ነበር። አፄ ዮሐንስ ሕዝባቸውን ሁሉ ክርስቲያን ሊያደርጉት ማሰባቸውን ደርቡሾች በሰሙ ጊዜ ሊወጉዋቸ ተነሡ። መጀመሪያ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወግተው መተማ ላይ ድል አደረግዋቸው። በመተማ ጦርነት ላይ ደርቡሾች ብዙ ኢትዮጵያውያን ገደሉ። በብዙ የሚቆጠሩ ቤቶችና ጎጆዎች አቃጠሉ።

ደርቡሾች ድል ማድረጋቸውንም አፄ ዮሐንስ በሰሙ ጊዜ በጣም ተናደዱ። ሙሉ ጦራቸውን ይዘው ወደ መተማ ዘመቱ። ወታደሮቹም ወደ ጦር ቦታ ሲሄዱ ለሃይማኖታቸው ላገራቸውና ለሕዝባቸው ደማቸውን ለማፍሰስ መቍረጣቸውን በፉከራና በሽለላ ይገልጹ ነበር። በመተማም የአፄ ዮሐንስ በጦርነቱ መካከል ቆስለው ሞቱ። ወታደሮችም በንጉሣቸው ሞት በጣም አዝኑ። በርትተው በመዋጋት ፋንታ ለቅሶንና ሐዘንን ተስፋ

መቅረጥንም በመንፈሳቸው አሳዩ። ደርቡሾች ግን በአፄ ዮሐንስ ሞት ኃይላቸው ሊበረታና አሸናፊነትን ሊያገኙ ቻሉ። በመጨረሻም ድል አድርገው የአፄ ዮሐንስንም አንገት ቆርጠው ወደ አገራቸው ተመለሱ። የአፄ ዮሐንስንም አንገት ለንጉሣቸው ለከዲፍ አበረከቱ። እንግሊዞችና ደርቡሾች ከዚያ በፊት ሲዋጉ አፄ ዮሐንስ ለእንግሊዞች ረድተው ስለ ነበር ደርቡሾች የጠላታቸውን ራስ በመቁረጣቸው ትልቅ ደስታና በዓል አደረጉ።

አፄ ዮሐንስም ከሞቱ በኋላ ጦራቸው መሪ በማጣቱ ተበተነ። መላው የትግሬና የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞታቸው አዘነ። አፄ ዮሐንስን የመሰለ ሃይማኖታዊና ብልኅ መሪ እንደማያገኙ ተሰማቸው።

## ጥያቄዎች

1. በኢትዮጵያ ካርታ ላይ አድዋ ሥላሴና አኩስም ጽዮንን በልዩ ቀለም ርሳስ አመልክት።
2. በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥትና በአሁኑ ጊዜ የምታየውን ርምጃ በመጠኑ አወዳድረው።
3. ደጃዝማች ካሣ ማንን በመርዳት ብዙ የጦር መሣሪያዎች አገኙ? ምክንያቱን ካምስት በማያንሱ መሥመሮች ግለጽ።
4. አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ከማን ቀጥለው ነገሡ? ዘመነ መንግሥታቸውስ በእንዴት ያለ ሁናቴ ተፈጸመ?
5. አፄ ዮሐንስ ከኢትዮጵያ ውስጥ እነማንን ለማስወጣት ቁርጥ አሳብ አደረጉ? ምክንያቱስ?
6. አፄ ዮሐንስ በኢትዮጵያ ለማስፋፋት የሚፈልጉት ምንድር ነበር?
7. ስለ አፄ ዮሐንስ ዕረፍት በአጭሩ ጻፍ።

# ዳግማዊ ምኒልክ

በኢትዮጵያ ከተነሡት ስመ ጥሩ ነገሥታት አንዱ ዳግማዊ ምኒልክ ናቸው። ዳግማዊ ምኒልክ ኢትዮጵያ የአንድ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በማድረጋቸው በጣም የታወቁ ናቸው። ዳግማዊ ምኒልክ በ1836 ዓ.ም ወገዳ ተወለዱ። እናታቸው ደግሞ ወይዘሮ እጅግአየሁ የመንዝ ባላባት ወገን ነበሩ።

ዳግማዊ ምኒልክ በተወለዱበት ጊዜ ኢትዮጵያ በተለያየችና እያንዳንዱም ጠቅላይ ግዛት በንጉሥ የሚገዛ ነበር። ንጉሦችም ግዛታቸውን ለማስፋፋት እርስ በርሳቸው ይዋጉ ነበር። በዚያን ጊዜ የጎንደር ንጉሥ የነበሩት አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ለመግዛት ምኞት ስለነበራቸው የሸዋን ንጉሥ ንጉሥ ኃይለ መለኮትን ወግተው ድል አደረጉ። ምንም እንኳን አፄ ቴዎድሮስ ንጉሥ ኃይለ መለኮትን ድል ቢያደርጉም ምኒልክን በአስተዋይነታቸውና በጠባያቸው ስለወደዷቸው ወደ ጎንደር ወስደው በደንብ አሳደጉዋቸው። ምኒልክ ወደ ጎንደር ሲሄዱ አሥራ አንድ ዓመታቸው ነበር። ከዚህም በላይ አፄ ቴዎድሮ ሴት ልጃቸውን ለምኒልክ እንደዳሩ ይነገራል።

ሆኖም ምኒልክ አባታቸውን ንጉሥ ኃይለ መለኮትን አፄ ቴዎድሮስ ድል ያደረጉ ጠላት መሆናቸውን ዘወትር ያስታውሱ ነበር። ስለዚህ ከመቅደላ አምልጠው የሚወጡበትን ዘዴ ሁልጊዜ ይፈልጉ ነበር። በመጨረሻ አንድ ቀን ማታ ከናታቸው ጋር ሆነው ከመቅደላ ጠፍተው ለመሸሽ ቻሉ። ከረጅም ጉዞ በኋላ ወደ ሸዋ ገቡ። ከዚህም በኋላ ብዙ ርዳታ ከሸዋ ሕዝብ ምኒልክ አግኝተው የሸዋ ንጉሥ ሆኑ። አፄ ዮሐንስም ምኒልክ አምጠው በመንገሣቸው በመደሰት የምሥራች ላኩላቸው። ከዚህም በላይ አፄ ዮሐንስ ሐረር ከፋና የጋላ አገሮች ሁሉ የንጉሥ ምኒልክ ግዛት መሆናቸውን አረጋገጡላቸው። ከዚህ በኋላ ምኒልክ ኃይላቸው የደረጀ ጎበዝ ንጉሥ ሆኑ። አፄ ዮሐንስም ሲሞቱ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ነኝ በማለት ተነሡ። በእንጦጦ ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ማቴዎስ ቅብዓ ነገሥት ተቀብተው ንጉሠ ነገሥት ሆኑ። የዘውዱም በዓል ጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም ነበር።

ከዚህ በኋላ ምኒልክ ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ትልቅና ኃይለኛ መንግሥት ለማድረግ ተነሡ። ስለዚህ ጠቅላይ ግዛቶች ህሉ በርሳቸው ሥር እንዲተዳደሩ ማቅናት ጀመሩ። በዚያን ጊዜ የኢጣልያ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር የምትጥር ጠላት ነበረች። አፄ ምኒልክም ኢትዮጵያን ጠላት እንዳያጠቃት በጣም የሚሠውላት ንጉሥ ነበሩ። ስለዚህ ኢጣልያን ለመውጋት ጠመንጃና የጦር መሣሪያ ገዙ። ከዚህ በኋላ ከኢጣልያ ጋር ጦርነት ገጥመው የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ላይ ግፉም በሆነ አኳኋን አፄ ምኒልክ ድል አደረጉ። የኢጣሊያ መንግሥት ጦር አዛዥ የነበረው ጄኔራል አልበርቶንም ማረኩት። በመጨረሻም ከሰሜን ኢትዮጵያ ጠላትን አስጡት። በኋላም በዚያን ጊዜ የኢጣሊያ ግዛት የነበረችውን ኤሪትሪያን አፄ ምኒልክ ወረው የአዲቀይህን ምሽግ ያዙ። አፄ ምኒልክ የኢጣሊያን መንግሥት ድል ከነሡት በኋላ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር ተስፋ ቆረጠች። በመጨረሻም የኢጣሊያ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር አፄ ምኒልክ የቆረቆሩት መናገሻ ከተማ በአዲስ አበባ የሰላም ውል አደረገች።

ከዚህ በኋላ አፄ ምኒልክ የኢትዮጵያን አስተዳደር አንድ ለማድረግ ማሻሻል ጀመሩ። በራስ መኰንን ርዳታ አፄ ምኒልክ ብዙዎቹን ጠቅላይ ግዛቶች አቅንተው ከርሳቸው ሥልጣን ሥር አደረግዋቸው። አፄ ምኒልክ የመንግሥቱን የአስተዳደር ሥርዓት ከፋፍለው በየሥራው ክፍል ሚኒቴር ሾሙ። ይህም ሲሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ ጊዜ ነው። ታማኝ አሽከሮቻቸውንም የየጠቅላይ ግዛቱ አገረ ገዥዎች አድርገው ሾሟቸው። በዚህ አኳኋን አፄ ምኒልክ የመንግሥታቸውን የአስተዳደር ሁናቴ ሊከተሉና ሊያውቁ ቻሉ።

ከዚህም በላይ አፄ ምኒልክ በውጭ አገር ጉዳይና በታላላቅ መንግሥታት የፖለቲካ ሁናቴ በጣም ይደሰቱ ነበር። ስለዚህ ራስ መኰንን ወደ ፓሪስና ልዩ ልዩ የአውሮፓ አገሮች ሄደው የአውሮፓውያንን ኑሮና ሥልጣኔ በዓይናቸው እንዲመለከቱና እንዲነግሯቸው አፄ ምኒልክ ላኩዋቸው። ከዚህ በኋላ አፄ ምኒልክ ከፈረንሳይ ከእንግሊዝ መንግሥታት ጋር ወዳጅነት አበጁ። ኢትዮጵያን ሊጎበኙ የሚመጡትን የውጭ አገር ሰዎች በደንብ ይቀበሉና ያስተናግዱ ነበር።

ዳግማዊ ምኒልክ ከዘመናቸው በፊት ተደርጎ የማያውቀውን ብዙ ነገር አደረጉ። በየጠቅላይ ግዛቱ ፍርድ ቤት አቋቋሙ። የኢትዮጵያን የፍርድ አመራር አሻሻሉ። አፄ ምኒልክ ድሃ ሕዝባቸው በደንብ እንዲኖር በጣም ያስቡና ይከታተሉ ነበር። አንድ ጊዜ አንበጣ መጥቶ የሕዝቡን እህል በልቶ ረኀብ ቢነሳ አፄ ምኒልክ ከራሳቸው ጎተራ እህል አውጥተው ሕዝቡን መገቡት።

ከዚህ በቀር የዘመናዊው የኢትዮጵያ ሥልጣኔ መሠረት የተባለው በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ነው። የሐዲድ መስመርና የስልክ ሽቦ እንዲዘረጋ አደረጉ። ይህ ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ ድረስ በአፄ ምኒልክ ዘመን የተዘረጋው የሐዲድ መስመር የኢትዮጵያ ውናአ የመመላሻና መገናኛ ነው። ዳግማዊ ምኒልክ ለመጀመሪያ ጊዜ ፖስታ ቤት አቋቁመው የራሳቸው ምስል ያለበት ቴምብር አወጡ።

በሰኔ ወር 1900 ዓ.ም ዳግማዊ ምኒልክ በጣም ስለታመሙ የዙፋናቸው ወራሽ ልጃቸው ኢያሱ መሆኑን አስታወቁ። በዚያን ጊዜ ልጅ ኢያሱ ዕድሜያቸው 13 ዓመት ነበር። ልጅ ኢያሱ ትልቅ እስቲሆኑ ድረስ ራስ ተሰማ ናደው ሞግዚት እንዲሆኑ ተመረጡ። በ1906 ዓ.ም ደጉ አፄ ምኒልክ ሞተው ልጅ ኢያሱ ዙፋኑን ወረሱ።

## ጥያቄዎች

1. የቤጌምድር ዋና ከተማ ማን ነው?
2. ቤጌምድር ከአዲስ አበባ በየት በኩል ይገኛል?
3. ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ የተነሡት ነገሥታት እነማን ነበሩ? በየት በየትስ ነገሡ?
4. በሥልጣኔ ርምጃ በኩል አፄ ምኒልክ አሻሽለው የፈጸሟቸው ምን ምኖች ናቸው?
5. አፄ ምኒልክ ምን ምኖች አዳዲስ መገናኞች ከፈቱ?
6. የአድዋ ጦርነት በሚል አርእስት አጭር ተራኪ ድርሰት ጻፍ።
7. በኢትዮጵያ ካርታ ላይ አፄ ምኒልክ ያቀኑአቸውን አገሮች ፈልገህ በመሥመር አያይዛቸው።
8. አፄ ምኒልክ በምን ምክንያት ደግ ተባሉ?

PRINTED BY THE COOPERATIVE EDUCATION PRESS

P9-231 Addis Ababa.

December, 1959Ethiopia

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY